በኢትዮጵያ ማህበረሰብ ልማት ካውንስል / የአፍሪካ ማህበረሰብ ማእከል ህብረተሰቡን ማእከል ያደረገ የኤች.አይ .ቪ /ኤድስ መከላከልና ትምህርት ፕሮጀክት ሲያስተዋውቅ በደስታ ነው።

ፕሮጀክቱ በሚከተሉት አምስት ዋና ዋና ተግባራት ላይ ያተኮረ ነው።

- ከአፍሪካ ማህበረሰብ አባላት ጋር በመተባበር የመስክ አገልግሎት ማዳረስ፤

- የኮንደም አጠቃቀምና ዝንባሌ አስመልክቶ በተናጥልና በቡድን ውይይት ማድረግ፤

- ያታና እድሜን መሠረት ያደረገ የቡድን ውይይትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማካሄድ፤

- በአካባቢያችን የሚገኙ ድርጅቶች፤ ተቋማት እና የንግድ ክፍሎች ለፕሮጀክቱ እገዛ እንዲያደርጉ ማበረታት፤

- ከአፍሪካ ማህበረሰብ አባላት ባህልና ወግ ጋር የሚስማሙ የትምህርት መረጃ ቁሳቁሶችን ማሰራጨ፡

## ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ምንድን ነው?

ኤች.አይ.ቪ. የተፈጥሮ ቅስም ሰባሪ ረቂቅ ህዋስ ነው። ኤች.አይ. ቪ. የሰው ደም ውስጥ በመግባት የሰውነት ተፈጥሮአዊ በሽታ የመከላከል አቅም በማዳከም ለኤድስ የሚያጋልጥ ቫይረስ ነው። ኤድስ የተለያዩ የህመም ስሜቶች ስብስብ (ሲንድረም) ነው። በኤድስ የተያዘ ሰው በወቅቱ ተመርምሮ የህክምና እርዳታና እንክብካቤ ካለገኘ በሽታው እየተባባሰ በመሄድ ለሞት ይዳርጋል።

ኤች.አይ.ቪ. እንዴት ይተላለፋል?
.....አንድ ሰው ኤች.አይ.ቪ. ይኑረው አይኑረው ሳይታወቅ የወሲብ ግንኙነት በመፈፀም፤
.....ንፅህናቸው ያልተጠበቀ መርፌ እና ሌሎች ስለታም መሳሪያዎች፤ አደንዛዥና አነቃቂ እፆችን ለመወጋት፡ ለንቅሳትና ለመሳሰሉት ጉዳዮች በጋራ መጠቀም፤
.....ኤች.አይ.ቪ. ካለባት እናት ወደ ልጅ በእርግዝና፤ በወሊድና እና ጡት በምታጠባበት ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል፤
...በአልኮሆል መጠጥ፤ በአደንዛዥ እና አነቃቂ እፆች ተገፋፍቶ ከቁጥጥር ውጭ በመሆን ጥንቃቄ ለጎደለው ወሲብ መገፋፋት፤ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## ቁልፍ



### ለጤናማ ህይወት

- ማንኛውም አይነት የወሲብ ግንኙነት ከማድረግ በመታቀብ፤
- ንፅህናው ያልተጠበቀ መርፌ በጋራ አለመጠቀም፤
- ለአንድ ጓደኛ ታማኝ በመሆን፤
- በአንድ መፅናት ካልተቻለ ደግሞ ማንኛውም አይነት የወሲብ ግንኙነት በሚደረግበት ወቅት ኮንደምን ሁል ጊዜ በአግባቡ በመጠቀም፤
- የኤች.አይ.ቪ.. ምርመራ በማድረግ የጤንነት ሁኔታ ማወቅ የወሲብ ጓደኛም ምርመራ እንድታደርግ /እንዲያደርግ/ ማበረታት፤

### ያስታውሱ!

- ኤች.አይ.ቪ. አፍሪካ ውስጥ እንዳልቀረ፤
- ኤች.አይ.ቪ. ያለባቸው ቀጫጭን ሰዎች ብቻ አይደሉም፤
- ኤች.አይ.ቪ. የሚይዘው ወጣቶችን ብቻ አይደለም፤

በተጨማሪ የሚከተሉትን ያስታውሱ!
• ኤች.አይ.ቪ. በወባ ንክሻ አይተላለፍም።
• ኤች.አይ.ቪ. ካለበት ሰው ጋር አብሮ በመኖር፤ በመብላት፤ በመጠጣት፤ በመጨባበጥ በመተቃቀፍ፤ ጉንጭ ለጉንጭ በመሳሳም እና የመፀዳጃ ቤት መቀመጫ በመጋራት ኤች.አይ.ቪ. አይተላለፍም፡